# ኢትዮጵያ ከድጡ ወደ ማጡ እየገባች ነው

ከይኩኖ መሰፍን
sgbtsait@gmail.com

## ክፍል አንድ

ከሁሉም አስቀድሜ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ዓለም የምትገኙ ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ሁሉ ከያላችሁበት የከበረና ልባዊ ሰላምታዬን ለማቅረብ እወዳለሁ።

ከዚህ ቀጥዬም እንደተለመደው ላለፉት ሶስት ወራት ያህል ለግል ስራ ጉዳይ በሀገር ውስጥ ቆይታዬ በተለያዩ አካባቢዎች ተዘዋውሬ ብዙ ነገሮችን ለመገንዘብ ችያለሁ። በአካል ተገኝቼ በዓይኔ ያየኋቸውንና የታዝብኩዋቸውን በሙሉ በዚሁ አጭር ፅሑፍ በዝርዝር ለማቅረብ ባልችልም ህዝቡ በተለይም በዲያስፓራ በባህር ማዶ የሚኖረውን ወገን ሁሉ ማወቅ አለበት ብዬ የዘገብኳቸውን ወቅታዊ ችግሮች በሚመለከት አንገብጋቢ በሆኑ ጉዳዮችን ብቻ በማትኮር አጠር ባለ መልኩ ለማቅረብ ሞክሬያለሁ።

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያን ጎብኝቶ የተመለሰ ወይም ስልክ ደውሎ ቤተሰቡን ያነጋገረ ሰው ሁሉ ስትጠይቁ በአመዛኙ የምታገኙት መልስ “ዛሬ ሀገሪትዋን ማን እንደሚያስተዳድራት አናወቅም። የሕግ ከለላና ዋስትና የለንም። ያለንን ችግር ለመፍታት ለማን አቤት እንደሚባል አይታወቅም። እንዲያው በደፈናው የኢትዮጵያን አድባር ነው እያስተዳደረን ያለው እንጂ ለኛ የሚሆን መንግስት ካጣን ውለን አድረናል”። የሚል እሮሮ ነው የምትሰሙት። እውነት ነው እኔም በሀገር ቤት የሶስት ወር ቆይታዬ በብዙ ቦታዎች በመዘዋወር በአካል ተገኝቼ በዓይኔ ያየሁትንና የሰማሁትን ነገር ህዝቡ ከሚለው የተለየ አይደለም። እንዲያውም ችግሩ ህዝቡ ከሚለው በላይ ነው። የሚገርመው ደግሞ በሄድክበት ቦታ ሁሉ የምትሰማው እሮሮና ስጋት አንድ ዓይነት ነው። ህዝቡ ለኛ የሚሆን መንግስት የለንም የሚል እሮሮ ለማሰማት የተገደደበት ዋና ዋና ምክንያቶችስ ምንድን ናቸው? : -

### 1. ስርዓቱ ከማንም ጊዜ በላይ ወደ ፍፁም አምባ ገነንነትና ሕገ አልበኝነት ተሸጋግረዋል

አሁን ያለው የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ላዩን ከውጭ ስንመለከተው በአሸብራቂ ቃላት ታጅቦ ጋብ ያለና የተረጋጋ ይመሰላል እንጂ ውስጡ ውስጡን መቼ እንደሚፈነዳ የማይታወቅ የተዳፈነ እሳት ሆኖ አስጊ ሁኔታ ላይ የደረሰ መሆኑን መረዳቱ የሚከብድ አይደለም። በእውነት ረሃቡንና የፓለቲካ ምሕዳሩን ብልሹነት ተደማምረው በህዝባችን ላይ የፈጠሩትን ድርብ ድርብርብ ችግር ከምንናገረው በላይ ነው። ስርዓቱ ከማንም ጊዜ በላይ ወደ ፍፁም አምባ ገነንነትና ሕገ አልበኝነት ስለተሸጋገረ በሕብረተሰቡ ላይ ያሉት ችግሮች ከሚሸከመው በላይ ሆኖበታል። በዚህ ምሬት ምክንያት ህዝቡ መሪ ድርጅት ባይኖረውም ከመንግስት ጋር ዓይጥና ድመት በመሆን በራሱ ተነሳሽነት በያለበት የሞት ሽረት ትግል እያካሄደ ይገኛል። በቅርቡ በኦሮሞ፣ በትግራይ፣ በአማራና በሌሎች ክልሎች የተነሱት የህዝብ ዓመፆች መነሻቸው የመብት ጥሰት፣ ዓፈናና ምሕዳረ ብልሹነት መሆናቸውን ሌላ ቀርቶ ራሳቸው ጠቅላይ ሚኒስተር ሀይለማሪያምም ሳይቀር ያመኑበትና የመሰከሩበት ጉዳይ ነው።

ህዝቡ ለውጥ ይፈልግ እንጂ በስልጣን ላይ ያለው የአቶ መለስ ራእይ ወራሽ ነኝ የሚል መንግስት ግን ያለፈውን ስር የሰደደ ችግር ከመድገም አልፎ አዲስ ራእይና የተሻለ የመፍትሄ ፓሊሲ ለማፍለቅ የሚያስችል ዓቅሙም ፍላጎትም የለውም። ጠቅላይ ሚኒስትሩ አቶ ሀይለማሪያም ስልጣናቸውን ተረክበው አሃዱ ብለው ስራ ሲጀምሩ በፓርላማ የህዝብ ተወካዮች ተገኝተው የነገሩን ነገር ቢኖር የአቶ መለስን ራእይ አደራ ጠባቂና ባለኩንትራት መሆናቸው እንጂ ከእርሳቸው የምንጠብቀው ሌላ አዲስ ለውጥ እንደሌለ አረጋግጠውልናል። ጠቅላይ ሚኒስተር ሀይለማሪያም ኢትዮጵያን የመሰለች ትልቅ ሀገርና 90 ሚሊዮን ህዝብ ለመምራት የታሪክ አጋጣሚ ቢያገኙም ቅሉ እንደ አንድ መሪ የራሳቸው የሆነ አሻራ ጥለው ለማለፍ የሚያስችላቸው አዲስ ራእይና ፓሊሲ እንደሌላቸው ነው የነገሩን ። በዚህ መሰረት መንግስት ሀገርን በአግባቡ ለማስተዳደርና በሀገሪትዋ ላይ ስር የሰደዱትን ቅራኒዎችንና ህዝባዊ ዓመፆችን ለመቆጣጠርና ለመፍታት ነገሮችን ሁሉ ከዓቅሙ በላይ የሆኑበት ይመስላል ። ስለዚህ መንግስት በአሁኑ ወቅት እየተላተመ ያለው ከለውጥ ፈላጊው ህዝብ ጋር ብቻ ሳይሆን ከጊዜም ጋር ጭምር ነው።

ዛሬ በኢትዮጵያ ስለፍትሕና ዳኝነት ሲነሳ በመጀመሪያ በአእምሮዋችን ላይ የሚደቀነው በየእስር ቤቱ የታጎሩትን እንደነ እስክንድር ነጋ፣ በቀለ ገርባ፣ አንዱለም አራጌ፣ ወ/ሮ አልጋነሽ (ሶስት ልጆችዋን ዛሬ መንገድ ላይ ተጥለዋል)፣ አብረሃ ደስታ፣ ዮናታን ተስፋየና ሌሎች በሽዎች የሚቆጠሩትን ታጋይ ወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለውን ስቃይና መከራ ነው። የነዚህ ታጋይ ወገኖች የክስ አመሰራረትና አፈፃፀም ስንመለከትም አንደኛ በፀረ ሽብር ሕግ ከታሰሩት ውስጥ አንድም ሰው በሕገ መንግስቱ ላይ ከተቀመጠለት መብትና ግዴታ የዘለለ ሕገ ወጥ ተግባር ሲፍፅም ነበር ተብሎ የቀረበ አንድም ማስረጃ አላየንም ። ሁለተኛ የታሰሩት ሰዎች በእጃቸው ከብዕርና

ከወረቀት በስተቀር ሌላ ጦር መሳሪያ ያልነበራቸው፣ ሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ ተከትለው የፍትሕ ጥያቄ ሲያቀርቡ የነበሩት ናቸው። ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ ነገር ግን በህወሓት/ኢሕአዴግ በፀረ ሽብር ሕግ እየተመነጠሩ በቂም በቀል ወደ እስር ቤት እየተወረወሩ ያሉት የህሊና እስረኞች የፍርድ ሂደት ስናይ ሰብአዊና ዜግነታዊ መብታቸውን የሚጥስ ጭካኔ የተሞላበት አካሄድ ነው። ተቃዋሚዎች ስለሆኑ ብቻ ሕገ መንግስቱን አይመለከታቸውም። መጀመሪያ በካድሬው ዓይን ውስጥ ይገባሉ። ከዚያም ሰበብ አስባብ ተፈልጎ የሚጠመዱበት ቀን ይመቻቻል። ቀጥሎም አስደንጋጭ በሆነ መልኩ በአፋኝ ሐይል ተይዘው በዱላ እየተደበደቡ እስር ቤት ይገባሉ። እስር ቤት ከገቡ በኋላም አሰቃቂ የሆነ የአካልና የስነ ልቦና ጥቃት ይፈፀምባቸዋል ። ይህን ሁሉ ስቃይ ካሳለፉ በኋላ ነው ወደ ማስረጃ ፍለጋ የሚኬደው። ከዚያም ሆን ተብሎ ማስረጃ እያፈላለግን ነው እየተባለ መቋጫ ለሌለው ጊዜ ፍርድ ሳያገኙ በእስር ቤቱ እንዲታሹና እንዲበሰብሱ ይደረጋል።

ሌላውን ትተን የዓረና ትግራይ ለሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ የአመራር አባልና የመቀሌ ዩኒቨርስቲ የፓለቲካ ሳይንስ ተመራማሪና መምህር የነበረው አቶ አብርሃ ደስታን የታሰረበትን ሁኔታና በፍርድ ሂደቱ የደረሰበትን ስቃይ ስንመለከት በሽዎች ወጣቶች የህሊና እስረኞች ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍና መከራ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ገላጭ ነው ብዬ አምናለሁ። ወጣት ምሁሩ አብርሃ ደስታ ለሰላማዊ ትግል ባለው ቆራጥነት : የፓለቲካ ብስለት : የማሳመን ችሎታና ልበ ሙሉነት ሽዎችን ወጣቶች ማነቃነቅ ሲጀምር የስርዓቱን ካድሬዎች በሃሳብ ሊመክቱትና ሊያሸንፉት አልቻሉም ። ስለሆነም “ ይህቺን ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም ” ከሚል ስጋት የተነሳ እሱም በተራው አፋኝ ስኳድ በማሰማራት እየደበደቡ እስር ቤት ወረወሩት። የታጋይ አብርሃ ደስታ መታሰር ለተቀሩት ታጋዮች በተለይም ለትግራይ ወጣቶችና ምሁራን “እኔን አይተህ ተቀጣ” የሚል አስደንጋጭና አስፈሪ መልእክት ለማስተላለፍ እንደ መቀጣጫ አድርገው ተጠቅመውበታል። መጀመሪያ በካድሬዎቹ ጥርስ ገብቶ በዓይነ ቁራኛ ሲከታተሉት ሰነበቱ። ከዚያም ስራ ቦታ ውሎ ወደ ቤቱ ሲገባ ትልቅ ሽፍታ የማረኩ ይመስል አፍነው በመያዝ ከደበደቡት በኋላ ወደ አዲስ አበባ ወስደው እስር ቤት አስገብተው ሲያሰቃዩት ቆዩ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ፍርድ ቤቱ ከተከሰሰበት የአሸባሪነት ወንጀል ነፃ የለቀቀው መሆኑን ቢታወቅም ቅሉ አፍ እላፊ ተናግረሃል ተብሎ እንደገና በእስር ቤቱ እንዲቆይ በማድረግ እንደልማዳቸው ይኸውና እስከ ዛሬዋ ቀን ድረስ ያላንዳች ፍትሕ በጨለማ ቤት ታጉሮ ይገኛል።

በግልፅ እንደሚታየው ዛሬ የህወሓት/ኢሕአዴግ መንግስት ስልጣኑን በሞኖፓል ተቆጣጥሮ ራሱ ሕግ አውጪ፣ ራሱ ዳኛ ፣ ራሱ ከሳሽ፣ ራሱ መስካሪ፣ ራሱ ፓሊስ፣ ራሱ አሳሪና ገራፊ ሆኖ በፈላጭ ቆራጭነት በቆመበት ሀገር የህዝብ መብትና ነፃነት ይከበራል ብሎ ማሰብ ፍፁም የዋህነት ነው። በተለይም ዓለምን ያስደመመ የ2007 ዓ.ም. ሀገራዊ ምርጫ በመላ ሀገሪቱ ሌሎቹ ተወዳዳሪዎችን በዜሮ በመዘረር መቶ በመቶ አሸነፍኩ ብሎ ካወጀበት ቀን ጀምሮ በህዝብ ላይ በተለይም እንደነ መድረክ፣ አንድነት፣ መኢአድና በመሳሰሉት ተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶች ላይ እየወሰደ ባለው ምሕረት የለሽ እርምጃ ምክንያት ባለፉት ጥቂት ወራት ብቻ ከ4000 በላይ አባላት በጀምላ እስር ቤት አጉሯል ። በመሬት ወረራ ሳቢያ በኦሮሚያ ክልል በተነሳው የመብት ጥያቄ ምክንያትም ከ300 በላይ የክልሉን ወጣት ተማሪዎች ተገድሏል ። በአስር ሽዎች የሚቆጠሩም እስር ቤት ታጉሯል፣ ቆስሏል፣ ተሰውሯል፣ አሊያም ሀገር ለቀው ሸሽቷል። ዛሬ ኦሮሚያ ከሲቪላዊ አስተዳደር ወደ ፓሊስ ሀገር (police State) ተቀይሮ የሽብርና የብጥብጥ ድባብ የነገሠበት ክልል ሆኖ ይገኛል። መንግስት ምርጫን መቶ በመቶ አሸንፍኩ ባለበት ማግስት ይህ ዓይነቱ ጭካኔ የተሞላበት የጀምላ እልቂት በኦሮሞ ህዝብ ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ አሳዛኝ ክስተት በመሆኑ የማይረሳ ጥቁር ታሪክ ጥሎ አልፏል ።

በኦሮሚያ የተፈፀመው አሳዛኝ ክስተት (ትራጀዲ) ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየን የህወሓት/ኢሕአዴግ ስርዓት ላለፉት አርባ ዓመታት ያህል የተከተለውን የከፋፍለህ ግዛ ኢንጂነሪግ የዘራውን እያጨደ መሆኑን ነው። ላለፉት ዓስርተ ዓመታት ህዝቡን እርስ በርሱ ለማናቆር ሲባል በብሄር ብሄረሰቦች መካከል የቀበረውን ፈንጅ እየፈነዳ መሆኑን ነው የሚያመላክተን። በ2007 ዓ.ም. ተወዳድሬ መቶ በመቶ አሸነፍኩ የተባለውን ምርጫ በህዝቡ ፍላጎት የተገኘ ውጤት ሳይሆን በአፈ ሙዝ ሀይልና በማጭበርበር የተገኘ መሆኑን የሚያሳይ ነው። የብሄር ብሄረሰቦችን ጥያቄም ስንመለከት ደግሞ ለስርዓቱ ከፋፍለህ ግዛ መሳሪያ እንዲሆን ተደረገ እንጂ ጥያቄውን በሀቀኛ ዴሞራሲያዊ ስርዓት ጥላ ስር ሆኖ በህዝቦች መፈቃቀድና እኩልነት ላይ መሰረት አድርጎ ያልተሰራ መሆኑን በግልፅ የሚያሳይ ነው። በቅርቡ ከቤንሻንጉል፣ ከጋምቤላና ከደቡብ የተባረሩትን የአማራ ወገኖቻችንም የሚያሳየን የስርዓቱ የከፋፍለህ ግዛ ውጤት መሆኑን ነው። በአንድ ወቅት ራሳቸው ጠቅላይ ሚኒስተሩ አቶ ሀይለማሪያም ደሳለኝ ሲናገሩ “በየክልሉ የኛ ቋንቋ የማትናገሩ ከሆነ ከዚህ ውጡ። ሀብት ማፍራት አትችሉም እያሉ በአንዳንድ ክልሎች ችግር እየፈጠሩ እንደሆነ ደርሰንበታል። ይህም ለሀገሪትዋ አንድነትና ድህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ ነው” በማለት በምሬት ሲገልፁ ተደምጧል ። ከዚህ ተነስተን ማለት የምንችለው - አንድ ዜጋ በማንኛውም የሀገሪትዋን ማዕዝናት ተንቀሳቅሶ ለመስራት፣ ሀብት ለማፍራት፣ ለመምረጥና ለመመረጥ የማይችል ከሆነና መብቱን በዘር፣ በቋንቋ፣ በሀይማኖትና በቦታ ከተገደበ ሀገር አለኝ!! ኢትዮጵያዊ ነኝ!! ማለቱ ትርጉሙ ምን ሊሆን ነው? ይህ ሁኔታ በዚህ ዓይነት ከቀጠለ ደግሞ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር አንድነትዋን ጠብቃ ለመኖር ምን ዋስትና ይኖራታል? የሚለውን ጥያቄ የዚሁ ትውልድ ትልቁ ፈተና ነው ብዬ አምናለሁ።

በመሆኑም በኦሮሞ ክልል የተነሳው ደም አፋሳሽ ጥያቄ መነሻው የአዲስ አበባ የካርታ ፕላን ሳይሆን ስርዓቱ እየተገበረው ያለው የአፈና: የመሬት ወረራና የከፋፍለህ ግዛ ፓሊሲ የፈጠረው የመብት ጥሰት መሆኑን ተደጋግሞ ተገልፀዋል። ችግሩ ከኦሮሞ ክልል አልፎ በሌሎች የሀገሪትዋን ማዕዝናትም የብዙ ህዝብ ልብ አሸፍቷል። በዚሁ ሁኔታ የተቀጣጠለው የህዝብ መነሳሳትና ዓመፅ የተደናገጡ የህወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎችም በቅርቡ በኦሮሞ ፣ በወልቃይት፣ በቅማንትና በሌሎች አከባቢዎች በስርዓቱ ቁንጮ ላይ የተነሳውን የህዝቡን የመብት ጥያቄ በአግባቡ ከመፍታትና መልስ ከመስጠት ይልቅ መልኩንና አቅጣጫውን በመቀየር በሌሎቹ ብሄሮች በተለይም በትግራይ ህዝብ ላይ ያነጣጠረ ጦርነት በማስመሰል ጠላት መጣብህ በሚል ሰበብ የጥላቻ መርዝ ሲረጩ ከርሚል። ለዘመናት አብሮውና ተፋቅሮው በመቻቻል ይኖር በነበረው ወንድማማች ህዝብ መካከል አላስፈላጊ መናቆርና መተላለቅን ለመፍጠር ሲባል በሰላም ወዳዱ የትግራይ ህዝብ ላይ እናሆ ዛሬም አዲስ የቅስቀሳ ዘመቻቸውን ጀምሯል። የዘመቻቸው ዋና አላማም የህወሓት መሪዎች የትግራይ ህዝብን መደበቂያ ዋሻ አድርገው ለመጠቀም የተቀየሰ ስልት መሆኑን የአደባባይ ሚስጢር ከሆነ ውሎ አድሯል።

## 2. ህወሓት በትግራይ ህዝብ ላይ እየወሰደ ያለው የቀቢፀ ተስፋ እርምጃዎች

### ህወሓት የትግራይ ህዝብንና የሰማእታቱን አደራ የበላ ድርጅት ነው

የትግራይ ህዝብ መራራ መስዋእትነትን ከፍሎ ከትግሉ ምን አገኘ? ለሚለው ጥያቄ በአጭሩ ለመመለስ በትግርኛ አንድ አባባል አለ። እሱም "ሃዳኒት'ያ ከልብስ ጨጉርን ኣብ ኣፋ ፅልእን ትርፋ" በአማርኛ ሲተረጎም "አዳኝ ውሻ ጠጉር በአፉ ጥላቻ ትርፉ" እንደሚባለው ነው። በአንድ ወቅት አቶ ስብሓት ነጋ ሲናገር "ከኤርትራኖች በላይ ታግለን ኤርትራን ነፃ እንድትወጣ አድርገናል" ብሎ በይፋ እንደተናገረ የሚታወስ ነው። እንደተባለውም በአስር ሽዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ለጋ ወጣቶች በሳሕል በረሃ ዘምተው ለኤርትራ ነፃነት የደም ዋጋ ከፈሉ። ነገር ግን የትግራይ ህዝብ ያገኘው ምላሽ ዳግም ጦርነትና ጥላቻ ነው። በተመሳሳይ መልኩ የህወሓት መሪዎች በትግራይ ልጆች መራራ መስዋእትነት አዲስ አበባ ቤተ መንግስት ደረሱ። ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ማን ስልጣኑን መከታ በማድረግ የሀገርንና የህዝብን ሀብት እየዘረፈ ለልጅ ልጆቹና ለዘመድ አዝማዱ የሚተርፍ ምርጥ ቢላ ቤቶችና ሰማይ ጠቀስ ፎቆችን ሰርቶ በተንደላቀቀ ንሮ እየኖረና እየለማ እንዳለና በአንፃሩ የማን ልጅ ደግሞ ወደ ስደትና ልመና ተዳርጎ እየደማ እንደሚገኝ በዝርዝር ለናንተ ማቅረቡ ለቀባሪ ማርዳት ይሆንብኛል። የትግራይ ህዝብ የታገለለትን አላማና የከፈለውን የመስዋእትነት ዋጋ ፍሬ ሳያስገኝ ቀርቶ ጥላቻ ብቻ ይዞ ነው የቀረው። ከሌላው ወገኑ ጋር በማበር በአገዛዙ ላይ ዳግም የመብት ጥያቄና አመፅ እንዳያስነሳ በመስጋትም ሆን ተብሎ እሳት በመጫር በኢትዮጵያውያን ወንድሞቹ ዘንድ ከህወሓት ጋር ተደምሮ በጥላቻና በጥርጣሬ ዓይን እንዲታይና ዙሪያውን ሁሉ በጠላት የታጠረ በማስመሰል ሳይወድ በግድ በፍርሃት ፀጥ ረጭ ብሎ እንዲገዛ ለማድረግ በጋሃድም ሆነ በስውር ላለፉት አርባ ዓመታት ያልተፈነቀለ ድንጋይ አልነበረም።

አላማውም ግልፅ ነው በአንድ በኩል የትግራይ ምድር ሌላ ሐይል ዘወር ብሎ የማይመለከታት፣ የህወሓት የማይደፈር ምሽግ፣ የካድሬ መፈልፈያና የመዘርፊያ የጓሮ አትክልታቸውን አድርገው ለመጠቀም ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በዚሁ አካባቢ ቀና ብሎ የሚያይና ለሙብቱ ጥያቄ የሚያነሳ ትግራዋይ እንዳይኖር ነው። በዚህ መሰረት ህዝቡን አንድ ለአምስት አደራጅተው መፈናፈኛ አሳጥተውታል። እርስ በርሱ ተከፋፍሎ እንዲባላ አድርገውታል። ከጎረቤቱና ከገዛ ወንድሙ ጋር አናከሰውታል። በፍርሃትና በጥርጣሬ ተሸማቅቆ እንዲኖር አድርገውታል። ከሁሉም በላይ ያሳዘነኝ: ያሳፈረኝና አንጀቴን የበላኝ ነገር ቢኖር ይህ በአትንኩኝ ባይነቱንና በጀግንነት ተምሳሌትነቱን የሚታወቅና ለደርግም ሆነ ለባዕዳን ወራሪዎች ያልተንበረከከ ታጋይ ህዝብ : ዛሬ በገዛ ሀገሩ በፍፁም አፈና ተይዞ በመለሳውያንና በሻዕቢያውያን እጅ ወድቆ በድርብ አለንጋ እየተገረፈ እናሆ ዛሬ ክፉኛ ሲደማ: አንገቱን ደፍቶ ዳግም ሲያለቅስ ማየቴ የሞት ሞት ፍዳ ነው።

አዎ!! "አትረፍ ያለውን በሬ ቆዳውን ለከበሮ ይውላል" እንደሚባለው ሁሉ ከአቶ መለስ ሕልፈትና እረፍት በኋላም ሚስኪኑ የትግራይ ህዝብ እፎይታ አላገኘም ። ዛሬም ይባስ ብለው ነጋ ጠባ ህዝቡን እየሰበሰቡ "የታላቁ መሪያችን የመለስ ዜናዊ ራእይና አደራ ለመቀበልና ለማክበር ቃል ኪዳን ግባ" እያሉ መውጫና መግቢያ በማሳጣት እያስጨነቁት ይገኛሉ። ከዚህም አልፈው የመለስ ዜናዊ ፎቶግራፍ በመንግስታዊ መሰሪያ ቤቶች ብቻ ሳይሆን በግል ንግድ መድብሮችና በጠላ ቤትም ሳይቀር እንዲለጥፍና እንደ ጣዖት እንዲያመልክ ጫና እየተደረገበት ይገኛል። በዚህ ብቻ አላበቃም ለታላቁ መሪያችን መለስ ዜናዊ ሐወልት መሰሪያ እየተባለ ከረሃብተኛው ህዝብ የሚሰበሰበው ገንዘብም ተጨማሪ ድብ ዕዳ የሆነበት ጉዳይ ነው ። ሌላ ቀርቶ የቀበሌ መታወቂያ እንኳን ለማውጣት እንደ የዜግነትና የነዋሪነት መስፈርት ተደርጎ የሚወሰደው ለመለስ ዜናዊ ሐወልት መስሪያ የሚሆን ገንዘብ ማዋጣትና ራእዩን መቀበል እንደ ቅድመ ሁኔታ ተደርጎ ይወሰዳል። ለማያነበው እና በወሬ ብቻ ለሚሰማው የድርጅቱ ልሳን የሆነ ጋዜጣም በግድ እንዲከፍል ይደረጋል። ካልተቀበልክ ደግሞ ሊደርስብህ የሚችለውን የአካልና የስነ ልቦና ቅጣት ምሕረት የለውም። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተንቀሳቀስኩበት ቦታዎች ሁሉ ያየሁት ነገር ደግሞ እያንዳንዷን ትንሽ ደን ያላት ቦታ ከተገኘ ሆን ብለው መለስ ፓርክ ተብሎ እንዲጠራ ይደረጋል። የዚህ ዓይነቱ ተግባር ምናልባት በሌሎች ክልሎች ይቀንስ ይሆናል እንጂ በትግራይ ምድር የተለመደ ጉዳይ ነው።

በአሁኑ ጊዜ በትግራይ የመልካም አስተዳደርና ፍትሕ ማጣት፣ የስርዓቱን አድልዎና አፈና ተደማምረው ህዝቡ ከሚሸከመው በላይ ሆኖበታል። ይህ ሁሉ ችግር የመኖርና ያለ መኖር የህልውና ጥያቄም እየሆነ ስለመጣ ህዝቡ ምሬቱን በግልፅ መናገር ጀምሯል። የህዝቡን መነሳሳት ያሰጋቸው እነ አባይ ወልዱም ዘላቂ መፍትሄ ከመሻትና ህዝቡን የሚያረጋጋ ስራ ከመስራት ይልቅ በእነሱ ላይ ያነጣጠረውን ጥያቄ መልሰው ወደ ህዝቡ በመወርወርና ግምገማ እያሉ በመስብሰብ እርስ በርሱ እየተባላ እንዲውል እያደረጉት ይገኛሉ። የህዝቡን ቀልብ ለመቀየር ሲባል ደግሞ ኦሮሞ ባንተ ላይ ተነስቷል ፣ በትግልህ ያገኘኸውን የወልቃይት መሬት ሊወስድብህ ነው፣ ወዘተ እያሉ ማደናገሪያ ስልቶችን በመደርደር ህዝቡ መሰረታዊ ጥያቄውን ወደ ጎን ትቶ ጊዜውን አላስፈላጊና አሰልቺ በሆኑት ጉዳዮች ላይ ተጠምዶ እንዲውል እያደረጉት ይገኛሉ። ይሁን እንጂ ዛሬ የትግራይ ህዝብ ጠላቶች ህዝብ አይደለም። ቀንድ ጠላቶቹ ለድህነት : ለውርደት : ለጦርነት : ለአስከፊ ስደት የዳረጉትና እንዲሁም ከኢጋም እንደተጠጋ ቁልቋል በሻዕቢያ እየደማ እንዲኖርና ሉዓላዊ ክብሩን በባዕዳን እንዲደፈር ያደረጉት በውስጡ የበቀሉ እሾኽ አሜኬላዎች መሆናቸውን ጠንቅቆ ያውቃል። ከዚህ የተነሳ በአሁኑ ጊዜ የትግራይ ህዝብ ዋነኛ ስጋት ህወሓት በህይወት አለ ወይስ የለም የሚል ጥያቄ አይደለም ። ህወሓትና የትግራይ ህዝብ ሆድና ጀርባ ከሆኑት ቆይቷል። የህወሓት መሪዎች የትግራይ ህዝብን መድህን : ከለላና ጠበቃ መሆን እንደማይችሉ በተግባር የታየ ስለሆነ ህዝቡ በነቂስ ያውቃል።

- ህወሓት የትግራይ ህዝብንና የሽዎች ሰማእታትን አደራ የበላ ድርጅት ነው። ይህ ማለት ህዝቡ የህወሓት መሪዎች የሰማእታትን ደም የተከፈለበት አላማ በመርሳት የግል ጥቅማቸውን በማሳደድ ላይ እንደሆኑ ያውቃል። ለምሳሌ ባለፈው ጊዜ በመቀሌ ተዘጋጅቶ በነበረው ፌስቲቫል ለመሳተፍ ከዲያስፓራ የመጡ ከ3000 በላይ የትግራይ ተወላጆች በተሰበሰቡበት አዳራሽ ላይ ከተሳታፊዎች አንዱ ያቀረበው ጥያቄ እንዲህ ይላል "እኔ ከሁሉም በላይ ያሳዘነኝና የሚያሳፍር ስራ በትግራይ ያየሁት ትናንትና ስንት ታጋዮችን ቀብረው የመጡና ስንት የደም ዋጋ የተከፈለበትን አላማ ሲመሩና ሲያስተምሩ የነበሩትን ሰዎች ዛሬ ወደ ግልፅ ሌብነት ተሰማርተው ስናይ ለህወሓት ብቻ ሳይሆን ለትግራይ ህዝብም ጭምር ከዚህ የከፋ ውርደትና ሐፍረት የለም " ብሎ አስተያዩትን ሲጨርስ አዳራሹ በጭብጨባ : በፍጩትና በጭኾት እንደተናጋ የምናስታውሰው ነው።

  በተመሳሳይ በቅርቡ ግምገማ በሚል አጀንዳ ከሁሉም የትግራይ ወረዳዎች ተጠርተው ከአንድ ሺሕ አምስት መቶ በላይ አባይ ወልዱን ጨምሮ ከፍተኛ የህወሓት መሪዎች፣ የህዝብ ተወካዮችና ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በመቀሌ በሐወልት አዳራሽ ላይ በተሰበሰቡበት ወቅት ያካባቢውን የኪነት አባላት በመተባበር በድራማ መልክ በትግርኛ ያቀረቡትን ምሬት የተላበሰ ዝግጅት የተሰብሳቢውን ቀልብ የሳበ እንደነበር ያሳያል። በመድረኩ ላይ የሚታየው በአንድ በኩል አንድ ልቡን በትዕቢት የተሞላ ባለስልጣን ወንበር ላይ ቁጭ ብሎ ዓይኑን አፍጥጦ ግራና ቀኙን ሲቃኝና ሲከራከር ይታያል። በሌላ በኩል ደግሞ በርከት ያሉ የኪነት ሰዎች አንድ በእንጨት የተሰራ ወንበር ተሸክመው ወደ አዳራሹ እያመላከቱ "የተከበራችሁ ህዝቦች ይህ የምታዩት ወንበር በእንጨት የተሰራ እንዳይመስላችሁ። የተሰራው በሰማእታት ደምና አጥንት ነው። ነገር ግን የሚገርመው የህዝባችን አደራ የበሉ ባለስልጣናት እዚሁ በሰማእታት ደምና አንጥንት የተሰራ ወንበር ላይ ቁጭ ብለው ነው የህዝብና የሀገር ሀብት እየዘረፉ የሚገኙት" ብለው ሲያቀርቡ አዳራሹ በተለያዩ ስሜቶች እንደተሞላ ቪድዮው ያሳያል። በነ አቶ አባይ ወልዱ ፊት የቁጣ መንፈስ ሲታይ በተራው ተሰብሳቢ ህዝብ ደግሞ የሃዘን ፊት ይታያል። ይህ ዓይነቱ የህዝቡን ስሜት የሚኰረኩር ቢጋሃድ የተቃውሞ ድራማ ሲቀርብ በህወሓት የአርባ ዓመት ታሪክ የመጀመሪያው ነው። እንዲያውም አንዳንድ ታዛቢዎች "ከድራማው በስተጀርባ ከውስጣቸው ሌላ ቡድን ሳይኖርበት አይቀርም" ብለው የሚተቹም አልታጡም።

- ህዝቡና ህወሓት ዓይጥና ድመት የሆኑበት ሌላው ምክንያት በዝርፊያ ላይ የተሰማሩት መሪዎች ዘላቂ ልማትና የፓለቲካ ለውጥ ያመጣሉ የሚል እምነት ያለው ትግራዋይ የለም። ልማት ለራሱ በነፃነት : በፍትሕና በእኩል ተጠቃሚነት መርህ ካልተደገፈ ውሎ አድሮ ዕድገት ሳይሆን ጥፋት ሊሆን እንደሚችል ጥርጥር የለውም። ለምሳሌ በኦሮሚያና በሌሎች አካባቢዎች የተነሳውን ዓመፅ ትተን በአሁኑ ጊዜ በሌሎች ሀገሮች እየተካሄደ ያለው አውዳሚ ጦርነት ያስከተለው እንደ ህንፃ: ድልድይ: ኢንዱስትሪ: መሰረተ ልማት: ማሕበራዊ መሰረት (social fabric) ውድመት፣ የህዝብ እልቂት: ወዘተ ስናይ መነሻው ልማት ስለሌለ አይደለም። መሰረታዊ መንሲኤው የሰላም ሞሶሶ የሆኑትን ፍትሕ: ነፃነት: የሕግ የበላይነትና ዴሞክራሲያዊ አስተዳደርን ስለጠፉ ብቻ ነው። ስለዚህ ሽሕ ፎቅ ቢሰራና ሽሕ ጊዜ ልማት እየተባለ ቢዘመር ህዝቡ የኔ ነው የሚለው መንግስትና ስርዓት ከሌለ ነገ ፈራሽ መሆኑን የሚያጠያይቅ አይሆንም።
- በልቡ የሸፈተ ህዝብ የህወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች የሀገርና የህዝብ ፍቅር አላቸው ብሎ በፍፁም አያምንም ። መሪዎቹ ከራሳቸው ጥቅም በላይ የህዝብ ጉዳይ ቅድሚያ የሚያዩ ቢሆኑ ኖሮ ሌላ ቀርቶ ህዝቡን ከአንድ ደካማ መንግስት ከሻዕቢያ ታጣቂዎች አደጋና ጥቃት እንኳን ሊያዱኑት ይችሉ ነበር። ነገር ግን አልሆነም። ምክንያቱ ጥቃቱ ድሃው ህዝብ ነው በየቀኑ የደም ዋጋ እየከፈለ ያለው እንጂ እነሱ አይደሉም። መሪዎቹ'ማ በተደላደለ ንሮና በመከላኪያ ጥበቃ ተከበው ስለሚኖሩ ጥቃቱ አጠገባቸው አይደርስም። እንዲያውም በተገላቢጦሽ ዛሬ እንደጠላት የሚያዩት የኤርትራ መንግስት ሳይሆን በሕጋዊ መንገድ ፈቃድ አውጥተው ሻዕቢያን ጭምር በሚቃወሙ ሀገር በቀል የፓለቲካ ተቃዋሚዎችን ነው ዱላቸውን ያነጣጠሩት። በተለይም የመለስ አደራ ጠባቂ ነን

የሚለው ቡድን የትግራይ ህዝብ እንዲዳከምለትና ፀጥ ረጭ ብሎ አንገቱን ደፍቶ እንዲገዛላቸው ነው የሚፈልጉት እንጂ ነፃነት አግኝቶ ቀና ብሎ ጥያቄ የሚያነሳ ህዝብ እንዲሆን አይፈልጉትም። ለምሳሌ እነ አባይ ወልዱ ከሻዕቢያ በላይ ጠላት አድርገው በዓይነ ቁራኛ የሚያዩት ዓረና ትግራይን ወይም መድረክን ነው። አቶ መለስ በህይወት ዘመናቸው ከኢሳያስ በላይ ጠላት አድርገው ሲመለከቱዋቸው የነበሩት እነ አቶ ገብሩ አስራት፣ እነ አረጋሽ አዳነና ሌሎች ናቸው። ለምን ቢባል አቶ መለስ በምንም መለኪያ ከነ አቶ ገብሩ አስራት የበለጠ ለትግራይ ህዝብ ስለሚሳሱለት አይደለም። ነገር ግን ዋናው ምክንያት እነ አቶ ገብሩ አምባገነንነትን አንቀበልም በማለት እኛም ለህገራችን ያገባናል ብለው የራሳቸውን መስመር ይዘው ትግል ስለጀመሩ ነው። ለአቶ መለስ ራስ ምታት ሆኖባቸው የቆየውም ይኸው ነው። ምክንያቱም ትግሉ እያየለና እየጎለበተ ከሄደ ለሌላው ወገን የእምቢተኝነትና የተቃውሞ አርአያ ይሆናሉ ብለው ስለሚሰጉ ነው።

- በአንድ የሰለጠነ ሀገር ውስጥ በሕብረተ ሰቡ ማኸል በመከባበርና በነፃነት ላይ የተመሰረተ ነፃና አማራጭ ሀይል ሲኖር ከሁሉም በላይ ተጠቃሚ የሚሆነው ህዝብ መሆኑን በብዙ ሀገሮች በተግባር የተፈተነ ሀቅ ነው። ጥራት ያለው ዕቃ የምታገኘው ውድድር ባለበት ገበያ ላይ ነው። ግለ መሪዎች ገደብ የለሽ ስልጣን ይዘው እንደ ፈለጉ በሀገርና በህዝብ ሀብት ላይ እንዳይባልጉ መቆጣጠሪያና የሀይል ሚዛን መጠበቂያ መሳሪያ አንዱ ጠንካራ ተፎካካሪ ሀይል ሲኖር ነው። አሁን ያሉት የህወሓት መሪዎች ግን የዴሞክራሲ መርህ እንኳን በአግባቡ የማይቀበሉ ብቻ ሳይሆን ራሳቸው የፃፉትን ሕገ መንግስት እንኳን በአግባቡ ተግባራዊ እንዲሆን ፍፁም አይፈልጉም። ተቃዋሚ ሀይል እንዲጎለብት በፍፁም የማይፈልጉበት ዋናው ምክንያት ደግሞ ለህዝብ አስበው ሳይሆን " ዋ " የሚላቸው አማራጭ ሀይል ካለ ብቻቸውን እንደፈለጉ መዝረፍና በስልጣን መባለግ እንደማይችሉ ጠንቅቀው ስለሚያውቁት ነው። ሕገ መንግስቱ በአግባቡ ተግባራዊ ከሆነ ደግሞ የያዙትን ስልጣንና የዘረፉትን ሀብት የሚነጠቁና በሕግ የሚጠየቁ መስሎ ስለሚታያቸው ስለሕግ ልዕልና ጨርሶ እንዲወሳም አይፈልጉም። በነፃ ውድድር ላይ የተመሰረተ ምርጫ እንዳይኖር የሚሰጉበትና በሩን የሚዘጉበት ምክንያትም አንዱ ይኸው ነው። ህዝቡ ሕገ መንግስታዊና ሉዓላዊ ስልጣኑን የሚያረጋግጥበት ከሁሉም የላቀ መብት ምርጫ መሆኑን እየታወቀና በሕገ መንግስቱ ውስጥ ተቀምጦ እያለ ነገር ግን በነፃ መድረክ ተወዳድረው ለማሸነፍ የፓለቲካ ካፒታልና የሞራል መሰረት የሌላቸው መሆናቸውን ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ካርዱን በአቋራጭ በአፈ ሙዝ ነጥቀው ለመውሰድ ይገደዳሉ።

## ሚዲያው መቶ በመቶ በአንድ ፓርቲ ቁጥጥር ስር ነው።

ሚዲያ በዛሬ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ከህዝቡ ንሮ ጋር ተቆራኝቶ እጅና እግር በሆነበት መዋእል ላይ አደንቁረህ ግዛ በሚል የስርዓቱን ፓሊሲ ምክንያት የትግራይ ህዝብ በአገሪተዋ ውስጥ ያሉና የሚደረጉ ነገሮች ሁሉ ነፃ ሚዲያን በመዝጋት የማወቅ መብቱን የተገደበ እና የተከለከለ ነው፡፡ በአንድ በኩል ሀገሪትዋ ለምታለች፣ ዕድገት አሳይታለች፣ አየተባለ ነጋ ጠባ ሲለፈፍ እንሰማለን። በሌላ በኩል ደግም ህዝቡን የዕድገት መሰረት የሆነውን ትክክልኛ የመረጃ ሐይል ተጠቃሚ እንዳይሆን በመከልከል ከሰለጠነ ዓለም የተጋረደ ህዝብ ሆኖ እንዲኖር እየተደረገ ነው። ስለዚህ ነፃ ሚዲያን መከልከል ማለት ወደ ዕድገት የሚወስድ መንገድ ሳይሆን ወደሗላ ወደ ጨለማ ዘመን የሚመልስ ስራ ነው እየተሰራ ያለው።

በትግራይ ያለው ሚዲያ ከአስተዳደሩ ጀምሮ በቀጥታ በህወሓት ማእከላይ ኮሚቴ የሚመራና መቶ በመቶ በአንድ ፓርቲ ቁጥጥር ስር የገባ ስለሆነ ህዝቡ ነጋ ጠባ ልማታዊ ጋዜጠኞች በሬ ወለደ ብለው በአሸብራቂ ቃላት ታጅቦ በሚያቀርቡት ድራማ ጆሮውን ከመደንቆር በስተቀር ሌላ በአካባቢው ያለውን ሁኔታ የሚያውቅበትና የሚያይበት አማራጭ መስኰት የለውም። አልፎ አልፎ እየወደቁም እየተነሱም ብዙ እንግልት እየደረሰባቸው ሲፅፉ የነበሩት አንዳንድ ነፃ ጋዜጠኞችም ከያሉበት እየተለቀሙ እስር ቤት ገብቷል አሊያም ወደ ውጭ ዓለም ተሰዷል። በሀገሪቱ ነፃ ሚዲያ የተፈቀደ ለማስመሰል በእጅ አዙር እየተደጎሙ ለመንግስት ሽፋኝ የሚሰጡ አንዳንድ ታማኝ ሰዎችም የሚያቀርቡት ፅሑፍ ሰርዓቱን የሚያወድስና ለአንድ ሞኖፓላዊ ፓርቲ ብቻ ያዳላ ከመሆን አልፎ በመሬት ላይ ያለውን እውነታና የህዝቡን ምሬት አንዳችም ሲዘግቡ አይታዩም።

በተለይም ከአቶ መለስ ሕልፈት በሗላ ህወሓት ተዳከሟል፣ ተበትነዋል፣ በትግራይ ህዝብ ዘንድ አሜኔታ አጥቷል፣ በሌላ አካባቢም የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶችንም ጨምሮ በኢትዮጵዮያ ህዝብ ዘንድ ተንቋል፣ ስልጣኑን ከተረከቡት መሪዎች ውስጥም መለስን የሚተካ ሰው የላቸውም፣ ሽባ አድርጎ ነው የተዋቸው፣ ወዘተ እየተባለ በሰፊው መወራት ከጀመረ ዓመታት አስቆጥሯል። በሀገሪቱ ውስጥ ያለው እውነታም ይህንን ሀቅ ነው የሚያረጋግጠው። እውነት ነው መለስ ህወሓትን ማዳከም ብቻ ሳይሆን ሊጠገን በማይችል መልኩ ነው ገድሎት የሄደው። መሪዎችም በመለስ ዙሪያ ተሰባስበው እሱ የሚያፈልቀውን ሀሳብና የሚሰጣቸውን ትእዛዝ ፈፃሚዎች ብቻ ስለነበሩ ከሕልፈቱ በሗላም እሱን ተከተው ለመስራትና አዲስ ፓሊሲ ቀርፀው ለመንቀሳቀስ የሚያስችላቸው ዓቅምም ሞራልም አላገኙም። እንዲያውም ነገሩን ሁሉ መላ ቅጡ ጠፍቷቸው በተለያዩ ጎበዝ አለቆች ተከፋፍለው እርስ በራሳቸው በጎሪጥ መተያየት መጀመራቸው የአደባባይ ሚስጢር እየሆነ መጥቷል። ከዚህ ስጋት የተነሳ ሚዲያውን ሙሉ በሙሉ በመቆጣጠር እንደነ ድምፅ ወያነ

ትግራይ፣ ጋዜጣ ወይን፣ የትግርኛ ቴሌቭዝን ፕሮገራምና ሌሎች ተለጣፊ የግል ጋዜጠኞችንም ጨምሮ በሙሉ ዓቅማቸው የህወሓትን ህላዌ በማረጋገጥና በማስተጋባት ህዝቡ ሌላ ነገር እንዳያስብና ሌላ አማራጭ ዜና እንዳይሰማ በነርሱም ፕሮፓጋንዳ ብቻ መወትወትና ማሰልቸት ነው ስራዬ ብለው የተያያዙት።

በተለይም በትግርኛ የሚተላለፉ ሚዲያዎች ነጋ ጠባ በየቀኑ ደጋግመው የሚያቀርቡት ዜና በዋናነት የሚያተኩረው አማራጭ አጥቶ ወደ ስደት ስለሚጎርፈው ወጣት : በየጎዳናው በልመና ላይ ተሰማርተው የትራፊክ ሙብራትን ያጣበቡት ህፃናትና ሽማግሌዎች: በየቀኑ በሻዕቢያ ታጣቂዎች ታፍኖ እንደ በጎች እየተነዱ ወደ ኤርትራ ስለሚወሰዱት ወገኖቻችን : ከትምህርት በዲግሪም ሆነ በዲፕሎማ ተመርቀው ስራ አጥተው በየመስሪያ ቤቱ ደጃፍ የሚኰለኰሉትና በየጎዳናው ስለሚርመሰመሱት የተማሩ ወጣቶችን : በረሃብ አለንጋ እየተገረፈ በምፅዋት ላይ ስለወደቀው ህዝባችን : ዜናች የተለየ አመለካከት ስለያዙ ብቻ እንደጠላት ተቆጥረው ከያሉበት እየተመነጠሩ ተወስዶው እስር ቤቶችን ያጣበቡ ወጣቶችን : በጠራራ ፀሐይ የሀገርንና የህዝብን ሀብት እየዘረፉ ወደ ባህር ማዶ ስለየሚያሻግሩ መሪዎችንና በአጠቃላይ የስርዓቱን ምሕዳረ ብልሹነትን በሚመለከቱ ተግባራት ላይ አንዳችም ነገር ትንፍሽ አይሉም። ጉዳያቸውም አይደለም። በሚዲያቸው ላይ ደጋግመው የሚናገሩት ትግራይ በህወሓት እንደተፈጠረች፡፡ ከህወሓት በቀር ሌላ አባት ድርጅት እንደሌላት፡ ሊኖራትም እንደማይችል፣ ሌሎች ሐይሎች በሙሉ አፍራሽ: ፀረ ልማት: ፀረ ሰላም: ፀረ ዴሞክራሲና ሳያፍሩም ፀረ አንድነት ናቸው ይላሉ፡፡

እንደ ሀቁ ቢሆን ኖሮ እነዚህ ሚድያዎች የሚተዳደሩት በህዝብና በሀገር ሀብት ስለሆነ ማገልገልና ቅድሚያ መስጠትም የነበረባቸው የሀገርንና የህዝብን ጉዳይ ነው። ነገር ግን "ውሻ በበላበት ይጮኧል ነውና" በየቀኑ ሳይታክቱ እንደቁራ የሚጮኹት የህዝቡን ብሶት ሳይሆን ለባለስልጣናቱ ጠበቃ በመሆን ነው። ለምሳሌ በተለያዩ ፕሮግራሞች ተደጋግሞ የሚቀርበው በመሪዎቹ ላይ ተስፋ የቆረጠውን ህዝብ ለማደናገር ሲባል ድሮ በትጥቅ ትግሉ ዘመን የነበረውን አውዳሚና የእርስ በርስ ጦርነት ታሪክ (recycle of painful history) በማቅረብ በአንድ በኩል ለሌላው ኢትዮጵያዊ "ቂማችንን አንረሳም። አንድ ነገር ብትሉ ይኸውና ዛሬም "ዋ" የሚል መልእክት ለማስተላለፍ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለትግራይ ህዝብ "ይኸውና ከሌሎች ጠላቶችህ ጋር በደም የተቃባን ስለሆነ እኛ ስልጣን ላይ ከሌለን ቂማቸውን መወጣጫ ትሆናለህ" የሚል የማስፈራሪያ መልእክት በማስተላለፍ ህዝቡ ወደደም ጠላም በእነሱ ባርነት ስር እንዲኖር ለማድረግ ነው። ይሁን እንጂ የጦርነት ታሪክ ሽሕ ጊዜ ቢወሳ አሁን ላለው የተራብ ትውልድ ዳቦ ሊሆነው አልቻለም። ዛሬ ህዝቡ የናፈቀውና አጥብቆ የሚጠይቀው ሰላም : ዳቦ: መሬት ላራሹ : ፍትሕ: ነፃነትንና የሕግ የበላይነትን ተረጋግጦ ያላንዳች ስጋት በሀገሪትዋ ውስጥ ከጫፍ እስከ ጫፍ ተንቀሳቅሶ ሰርቶና አምርቶ ለመኖር የሚያስችለውን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲኖር ብቻ ነው።

## የወጣቱን ፍልሰትና ሌሎች ማሕበራዊ ቀውሶች

ስለወጣቱ ተደጋግሞ የምንሰማው ወሬ በሊቢያ ይህን ያህል ታረዱ፣ ብዙ ወጣቶች በሜዲተራኒያንና በቀይ ባህር ሰጠሙ፣ በሲናይ በረሃ በውሃ ጥም ደርቀው ቀሩ፣ በሳሃራ በረሃ ለአውሬ ተዳረጉ፣ ከአገር ወደ ሀገር ሲሻገሩ ድንበር ላይ ተይዘው ታሰሩ፣ በዘራፊዎች ታገቱ፣ ለኩላሊት ንግድ ተዳረጉ፣ በታጣቂዎች ታፍነው ተወሰዱ፣ ከተሰደዱበት ሀገር ተባረው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ፣ ወዘተ ሲባል ስትሰማ የሚዘገንን ቢሆንም "እነዚህ ወጣቶች ሞት እንዳለ እያወቁ ለምን ስደትን: ውርደትንና ስቃይን ይመርጣሉ?" የሚል ጥያቄ ነበረኝ። አንዳንድ ጓደኞቼም በተመሳሳይ "ሀገር ለምቷል በተባለበት ሰዓት ለምንድን ነው ይህን ያህል ወጣት ወደ ውጭ የሚፈልሰው?" የሚል ጥያቄም ያነሱ እንደነበር አስታውሳለሁ። በተለያየ ጊዜ ለተለያየ ጉዳይ ወደ ሀገር ቤት ሄጀ ሁኔታውን በዓይኔ ካየሁት በኋላ ግን ለጠየቅኩት ጥያቄ በቂ መልስ ለማግኘት ችያለሁ።

አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከጠቅላላ ሀገሪትዋ ወደ ስደት ከሚፈልሰው ወጣት 40 ከመቶ የሚሆነው ከትግራይ እንደሆነ ያረጋግጣል። ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያትም ከማንም በላይ አፈናው፣ አድልዎና ስራ አጥነት በትግራይ ሰለሚበዛ ነው። ይህ የህወሓት ትውልድ ገዳይ ፓለሲ አምራች ሀይሉንና የተማረውን ወጣት ወደ ስደት እንዲፈልስ ብቻ ሳይሆን ለነገ ሀገርን የሚረከብ ጤናማ ዜጋ እንዳይፈጠር እያደረገ ይገኛል።

ወጣቱን ትክክለኛ የሀገርና የወገን ፍቅር ሰንቆ፣ ኢትዮጵያዊ ማንነቱን ተላብሶ፣ አኩሪ ባህሉን ታሪኩን ብሄራዊ እሴቶቹን ወራሽ በመሆን የነገ ተስፋና ተኪ ሆኖ በስነ ስርዓት ተኰትኩቶ እንዲያድግና እንዲገነባ የሚያደርግ ሕሃላፊነት የሚሰማው መንግስት የለም። ሩቅ ሳንሄድ ዛሬ በትግራይ በሞኖፓል በተያዙት የሚዲያ አውታሮች በትግርኛ በሚዘጋጁ ፕሮግራሞች ላይ የሚተላለፈው ዜና ይህችን ሀገር በደማቸውና በአጥንታቸው ገንብተው ስላቆዩልን የአባቶቻችንና የአያቶቻችን ታሪክና ማንነት አይደለም እየተማረ ያለው። በአንፃሩ ሀገርን የሚያፈርስና የሚበታትን የጦርነት ታሪክ ነው ነጋ ጠባ እንዲያይ እየተደረገ ያለው። ይህ ብቻ አይደለም የትግራይ ህዝብ ወርቃማ ታሪኩን በማንቋሸሽና በመበረዝ ልክ ትግራይ በደደቢት በመለስና በህወሓት የተፈጠረች ፣ ህዝቡም ከህወሓት ሌላ እናት አባትና መድህን እንደሌለው፣ ሌላው ታሪካዊ ጠላቱን እንደሆነና እንደማይተኛለት፣ ህወሓት ዘላዓለም በስልጣን ላይ ከሌለ

ህዝቡም አብሮ እንደሚጠፋ በማስመሰል ነው ለጋ ወጣቱን እየተማረ ያለው። እንዲያውም ከሁሉም በላይ የሚገርመኝና ለሀገራችን የወደፊት ዕድልና አንድነት አስጊ መስሎ የታየኝ በወጣቱ ላይ እየተበራከተ የመጣው የግንጠላ አመለካከትን ነው። በየአካባቢው አልፎ አልፎ በምሬትም በጨዋታ መልክም የምትሰማው "መገንጠል የተሻለ አማራጭ ነው" ብለው በግልፅ የሚናገሩ ወጣቶች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።

ሌላው ለወጣቱ ፍልሰት ምክንያት እየሆነ ያለው በሀገሪቱ ላይ የተፈጠረው ዓይን ያወጣ ጭቆና: አፈና: አድልዎና ስራ አጥነት ናቸው። እነዚህ ሁሉ ተደማምረው ሀገሪትዋ ከምትሸከመው በላይ ሆኖባታል። የህወሓት አባልና ታማኝ ካልሆንክ ስራ ጥቅማ ጥቅምና እርዳታ የማግኘት ዕድልህ የተዘጋ ነው ብቻ ሳይሆን እንደዜጋ በነፃነት የመኖር መብትህም የተነፈገ ነው። የስራ ዕድል በሞያ ሳይሆን በታማኝነት ነው። ስለዚህ ወጣቱ ያለው ዕድል ወደ ስደት መፍለስ: ለልመና: ለጎዳና ተዳዳሪነት: ለሴተኛ አዳሪነትና ሌሎች አደንዛዝ ነገሮችን መዳረግ ነው። ይግረማችሁ በመላ ሀገሪቱ ውስጥ ጥቃቅን የንግድ ቤቶች ከሚባሉት ውስጥ እንደአሸን የፈሉት የጫት: የሐሽሽና የሸሻ ቤቶች ናቸው። አብዛኛው ወጣት በድግሪ የተመረቁም ሳይቀር የነዚህ የሱስ ንግድ ቤቶች ደንበኞች ናቸው። ወደ ውጭ ለመሰደድ ከተዘጋጁት አንዳንድ ወጣቶች አግኝቼ ሳነጋግራቸው የሰጡኝ መልስ "እኛ ከአስር ዓመት በላይ ተምረን እዚህ ያለ ስራ የሀገርና ወላጆቻችን ሸክም በመሆን የህሊና እስረኞች ሆነን እዚህ ከምንኖር የፈለገው ይምጣ ውጭ ሄደን መሞትን እንመርጣለን" የሚል ነው። አንዳንዶቹም አንድ ጊዜ ሁለት ጊዜ ዲፓርት ተደርገው እንደገና ተመልሰው ወደ ተባረሩበት ሀገር ይሄዳሉ። ከዚሁ ከስደት ጋር ተያይዞ በሕብረተ ሰቡ በተለይም በገጠር በገበሬው አካባቢ እንደ ቀልድ በእናቶቸ ዘንድ የሚነገሩ የብሶት መገለጫዎች ናቸው በማለት እዚህ ስሙን ለመጥቀስ ያልፈለግኩት አንድ ወጣት የነገረኝን ልጥቀስላችሁ "ጭነቱ ከበደኝ የልጅ ልጅ ፍዳ: ያልታደለች እናት አትድርም ወልዳ: ማን ይክፈልልኝ ማዳበሪያ ዕዳ: ወንድ ከወለድኩኝ ወደ ከናዳ: ሴት ከሆነች ትሂድ ወደ ጅዳ" የሚል ነው። ሌሎችም አሉኝ ሌላ ጊዜ አቅርብላችኋለሁ።

ከዚሁ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች ጋር በተያያዘ አንድ ምሳሌ ላክልና ወደ ሌላ ነጥብ ልለፍ። ባለፈው ጊዜ በትግራይ ተዘጋጅቶ በነበረው ፌስቲቫል ለመሳተፍ የመጡ ከሶስት ሺሕ በላይ የዲያስፓራ የትግራይ ተወላጆች በመቀሌ ከተማ በሰማእታት ሐወልት ተሰብስበው በነበሩበት ወቅት ለባለስልጣናቱ ካቀረቧቸው ጥያቄዎች ውስጥ "ሀገሪትዋን ለምታለች ገበሬውም ሀብታም ሆኗል ሲባል እንሰማለን። እውነት ልማት ካለ ለምን አምራችና የተማረው ወጣት ወደ ስደት ይፈልሳል? ለምን ብዙ ለማኞች በየጎዳናው ይታያሉ?" ብለው ሲጠይቁ የክልሉ አስተዳዳሪ አቶ አባይ ወልዱ ሲመልስ "እነዚህ የምታዩዋቸው ለማኞች እውነተኛ ለማኝ እንዳይመስላችሁ ስራ መስራት የማይፈልጉ ሰነፎች ናቸው" በማለት እንደተናገረ ይታወሳል ። አቶ አባይ ንግግሩን በመቀጠል "ለማኞቹ ከአንድ አካባቢ ብቻ የመጡ ናቸው" ሲል ያለ ሃፍረት ተናግረዋል።

ይገርማል!! የህወሓት መሪዎች የራሳቸውን ልጆች ወደ ውጭ እየላኩ በምርጥ ትምህርት ቤቶች ሲማሩ፣ የሀገርንና የህዝብን ሀብት በጠራራ ፀሐይ እየዘረፉ ለልጅ ልጆቻቸውንና ለዘመድ አዝማዳቸውን የሚተርፍ ምርጥ ቢላ ቤቶችና ሰማይ ጠቀስ ህንፃዎች ሰርተው በተንደላቀቀ ንሮ ሲኖሩ፣ የህወሓት ታማኝ የሆነውን ካድሬ ከህዝብና ከሕግ በላይ በመሆን የተለየ አመለካከት ያላቸውን ዜጎች እየኮረኮመ በማሳደድ ለራሱ ብቸኛ የልማት ተጠቃሚ ሆኖ ሲኖር በአንፃሩ የድሃው ህዝብ ልጅ ግን ዕጣ ፋንታው ስደት፣ ልመናና ጎዳና ተዳዳሪነት ሆኗል። ነገር ግን አቶ አባይ ወልዱ ይህንን ሀቅ በመካድ ዓይናችሁን በሻሽ ጨፍኑና እናሞኛችሁ በማለት ያቀረበው ንግግር ከአንድ መሪ የማይጠበቅ ፣ ከሀላፊነትና ከሙያዊ ስነ ምግባር ውጭ ከመሆኑም በላይ የራስህን ዜጎች ሞራል የሚነካና የሚያንቋሽሽ ፀያፍ ነው በማለት በርካታ ሰዎችን ቅር አሰኝቷል። ለነገሩ የሀገርን፣ የህዝብን ልዕልናና መብት የዶሮን ያህል ክብር የማይሰጡ፣ ጭንቅላታቸውን በትዕቢትና በፍቅረ ንዋይ የተሸፈኑት መሪዎች በህዝቡ ፊት ይህ ዓይነቱ ድፍረት የተሞላበትን ንግግር ቢያደርጉ የተለመደ ነውና ለብዙዎቻችን አዲስ ነገር ላይሆን ይችላል። እዩት ተመልከቱት!! ህሊናችሁም ይፍረድ!! እነዚህ ናቸው ትንሽ ይሉኝታ እንኳን ሳይሰማቸው በአደባባይ ቆመው ለጆሯችን እስከሚሰለቸን ድረስ ያለፈውን የአውዳሚ ጦርነት ፊልም እያሳዩ የትግራይ ህዝብ ነፃ አውጪ ነን ብለው የሚነግሩን።

## የሀገራችንና የህዝባችንን ድህንነት፣ አንድነትና ሉዓላዊነት አደጋ ላይ ነው

የሀገራችንን ድህንነት ጉዳይ በሚመለከት የቀድሞ የህወሓት/ኢሕአዴግ ከፍተኛ የአመራር አባልና የትግራይ ክልል አስተዳዳሪ የነበሩት : ዛሬ የዓረና መድረክ መስራችና የአመራር አባል በመሆን በማገልገል ላይ የሚገኙት አቶ ገብሩ አስራት በቅርቡ "ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ " በሚል ርእስ የፃፉትን ግዙፍ መፅሐፍ ሁለት ጊዜ ደጋግሜ አንብቤዋለሁ። በመፅሐፉ ከሰፈሩት ዓበይት ምዕራፎች አንዱ በአቶ መለስ የሚመራውን ህወሓት በህይወት ዘመናቸው 90 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብን በማግለል በኢትዮ-ኤርትራ ጉዳይ ላይ በጓሮ በኩል በነፃነታችን ላይ የተፈፀመውን ክሕደት በዝርዝር አስፍሯል። መፅሐፉ ያለፈውን ታሪክ ብቻ ያሰፈረ ሳይሆን ለወደፊቱም የኢትዮ-ኤርትራ ጉዳይ በህዝቡ ባለቤትነትና ቀጥተኛ ተሳታፊነት ለሁሉም ህዝቦች ዘላቂ ሰላምና ብሄራዊ ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ የማያዳግም እልባት ካልተገኘለት ለመጪው ትውልድም የሚተርፍ የተዳፈነ እሳት ሆኖ መቀጠሉ የማይቀር መሆኑን አስምሮውበታል። አቶ ገብሩ አስራት ባለፉት ዓመታት በብሄራዊ ጥቅማችን ላይ የተፈፀመውን ታሪካዊ በደልና ገመና

በመግለጥ ብዙ ኢትዮጵያውያን ሀቁን እንዲያቁት በማድረጋቸው በሚሊዮኖች ዘንድ በር ከፋች ሐርበኛዊ  አባት ተብለው እንዲጠሩ አስችሏቿል። ይህ ትውልድ ተሻጋሪ የሆነ መፅሐፍ በማቅረባቸውም ለብዙ ሰዎች ብርታትን : ወኔንና መነቃቃትን ከመፍጠሩም በላይ ድፍረትን: ሀቀኝነትንና ስብእናን አስተምሯል።

አንዳንድ መፅሐፉን ያነበቡ ግለሰቦችም " <u>የእግዚሄር ስራ በመፅሐፍ ቅዱስ የህወሓት ጉድ በአቶ ገብሩ ይገለጣል</u> " ተብሎ እንደተተቸ ሁሉ በዚሁ የተናደዱና የደነገጡ እንደነ አቶ ስብሓት የመሳሰሉት የህወሓት መሪዎች "አቶ ገብሩ ይህን መፅሐፍ መፃፉ ራሱን በራሱ የመግደል (ሱሳዳል) ፈፅሟል" ሲሉ እንደተናገሩ እናስታውሳለን። እንደነ ጀነራል አበበ ተክለሃይማኖት ደግሞ ፅሑፉ ምን እንደሚል እንኳን በአግባቡ ሳይረዱና ሳያነቡ "የአቶ ገብሩ መፅሐፍ የትግራይ ህዝብ ጠላቶችን ለማስደሰት ተብሎ የተፃፈ ነው" በማለት ከስነ ምግባር ውጭ በሆኑ የስድብ ቃላት የታጀበ: በግል ቂም በቀል ስሜት የተነዳ: ጭብጥ የሌለው: ከአንድ ምራቁን የዋጠ ሰው የማይጠበቅ  ትችት አቅርበው እንደነበር በትዕዝብት የምናስታውሰው ነው።

አሁን ያለው የሀገራችን ሉዓላዊነት : የህዝባችን ድህንነትና አንድነት ስንመለከት አቶ ገብሩ ካስቀመጡት የተለየ አይደለም። ሁኔታው ከመቼው ጊዜ በላይ ጥያቄ ውስጥ የገባበትና ባለቤት ያጣበት ሁኔታ ላይ ነን ያለነው። ስጋቶቻችንም በሶስት ነጥቦች ከፍለን ማየት እንችላለን። አንዱና ትልቁ ስጋት በውስጣችን ያለው የእርስ በርስ አለመተማመንና የመናቆር አዝማሚዎች ናቸው። ሁለተኛው ስጋት ደግሞ መንግስትና ህዝብ ዓይጥና ድመት ሆነው በተፋጠጥ የቆምበት ሁኔታ ብቻ ሳይሆን በስልጣን ላይ ያለው ስርዓት ውስጡን ተከፋፍሎና በስብሶ ነገሮች ሁሉ ከዓቅሙ በላይ ሆኖ ወደ ፍፁም አምባገነንነት የተሸጋገረበት ወቅት ስለሆነ ነገ ምን ዓይነት ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል አናውቅም። ስለዚህ ይህን ጉዳይ በአግባቡ ተረድቶ ህዝቡን ለጋራ ችግር በጋራ ለመፍታት በአንድ ጥላ ስር አሰባስቦና አስተባበሮ ሀገራችንን ከጥፋት ሊያድን የሚችል ሀይል ማን ነው? የሚል ትልቅ አጠያያቂ ጉዳይ ሆኗል። ሶስተኛው ስጋት ደግሞ በአካባቢያችን ያለው ጂኦ ፓለቲካዊ ትርምስ ለኛ ለሀገራችን ያለው ትርጉም ምንድን ነው? የሚለው ነው።

ኤርትራን ጨምሮ ጠቅላላ የቀይ ባህር ቀጠና ኢትዮጵያን በዓይነ ቁራኛ የሚመለከቱት በዓረቦች ቁጥጥር ስር ገብቷል ። በመሆኑም ኤርትራን ከኢትዮጵያ ገንጥለው ዓረባዊት ሀገር ለማድረግ የነበራቸውን የረጅም ጊዜ ሕልም ዕድሜ ለአቶ መለስ ዜናዊና በፔትሮ ዶላር አፋቸውን የተሸበቡ ወኪሎቻቸው በፈፀሙት ታሪካዊ ስሕትት ምክንያት እኖሆ ዛሬ ሀገራችን ሁነኛ ባለቤት በማጣት፡ የእርስ በርስ ንትርክ: የአፈናና የዝርፊያ መንደር ሆና መቅረቷን በውል የተገነዘቡት ዓረቦች ደካማነታችንን እንደ ታሪካዊ አጋጣሚ በመጠቀም እኖሆ ዛሬ አላማቸው ግቡን መቷል። "<u>በሞኝ ደጃፍ መፎር ይቆረጣል" </u>እንደተባለው ሁሉ በመሬት ስፋቷና የህዝብ ብዛቷ የኢትዮጵያን አንድ አስረኛ የማትሞላ የተባበሩት ዓራብ ዑመሬት የአባቶቻችን አጥንት በተቀበረበትና በቀይ ደማችን ተጠብቆ የኖረውን ቀይ ባህር በዓሰብ ወደብ ላይ የአየር ክልላችንም ጭምር መቆጣጠር በሚችል መልኩ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደላደለ ወታደራዊ ምሽግ በራፋችን ላይ ተክሏል። ይህ ሁኔታ በዚሁ ዓይነት ከቀጠለ ደግሞ የሀገራችን የነገው ዕጣ ፋንታ ምን ሊሆን ይችላል? የሚለውን እንቅልፍ የሚነሳ ጥያቄ እንድታነሳ የሚያስገድድ ሁኔታ ላይ ነን ያለነው።

በማጠቃለል ከዚሁ ክፍል አንድ ፅሑፍ የምንገነዘበው ትልቁ ጉዳይ ዛሬ ሀገራችን ከመቼው ጊዜ በላይ ከድጡ ወደ ማጡ እየገባች እንደሆነ ነው። ለዚህ ሁሉ ችግር ተጠያቂ ማን ነው? ለሚለው ደግሞ በኔ እምነት በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ብቻ አይመስለኝም። ምክንያቱም የሀገር ባለቤት መንግስት ሳይሆን ህዝብ ነው። ባለቤቱ አውቆ ከተኛ ደግሞ ይቅርና ሀይለኛ የሆነ ወራሪ ደካማም ቢሆን በኛ ላይ መዝመቱና ማላገጡ አይቀርም። ስለዚህ ስህተቱ ራሱን ፈቅዶ እጁን የሰጠና ለባርነታዊ አገዛዝ ራሱን ያመቻቸ ትውልድ የፈጠረው ዝምታ ነው የሚል እምነት አለኝ። ይህ አባባል ምን ማለቴ እንደሆነ በሚቀጥለው ክፍል ሁለት ፅሑፌን በዝርዝር ይቀርባልና እስከዚየው ድረስ በቸር ሰንብቱልኝ።

**እግዚአብሄር የኢትዮጵያን ሰላምና አንድነት ይጠብቅ**